
# እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20/2017 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት የኦክቶበር ሁለተኛው አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠርና መስፋፋት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በሰሜንና በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያ ክፍሎች እየተዳከሙ በመምጣታቸው ለጥቂት ቀናት ከተስተዋለው ቀላል ዝናብ በስተቀር በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ የተስተዋለባቸው ሲሆን፤ በአንፃሩ ወደ ምዕራብ አጋማሽና ወደ ደቡባዊ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ እንደቀጠለ መረጃዎች ያሳያሉ። በተጨማሪም በጥቂት የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ክፍሎች ላይ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል። ከባድ ዝናብ ከተመዘገባበቸው ሥፍራዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በጅንካ 51.3፣ በቡለን 51.1፣ በሻውራ 32.2፣ በግምቢ 43.9፣ በማጂ 50.0፣ በሊሙገነት 38.6፣ በጨዋቃ 55.4፣ በኢጃጂ 33.2፣ በበደሌ 34.8፣ እንዲሁም በጭራ 38.9 በሚ.ሜትር ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ25-188 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር፣ የምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ እንዲሁም አዊ ዞን፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ጋምቤላ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከፋ ዞኖች፣ ቤንች ማጂ፣ የደቡብና ሰሜን ኦሞ፣ የሲዳማ ዞኖች እንዲሁም የሰገን ህዝቦች፤ ከኦሮሚያ የምስራቅና የምዕራብ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራና ጅማ፣ የቦረናና የባሌ የደቡብ መዕራብ ዞኖች ከ4-10 ቀናት ያህል ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ የደቡብ ትግራይ፤ ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ወሎ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የጉራጌና የሀዲያ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ የሰሜንና የምዕራብ ሸዋ፣ አዲስ አበባ የአርሲና የባሌ ሰሜናዊው ክፍል፣ የምዕራብና የምስራቅ ሀረርጌ ዞኖች እንዲሁም አብዛኛው የሶማሌ ዞኖች ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-4 ቀናት ያህል ያገኙ ሲሆን፤ ተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከ5ሚ. ሚ.ሜ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2)።

ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛ ጋር ሲነጻጸር የደቡብ ትግራይ፤ አባዛኛው አማራ፤ ከአፋር የዞን 1፣4ና 5፣ የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ፤ ከጋምቤላ ጋምቤላ ዞን1ና 2፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከጉራጌና ከሀዲያ ዞኖች በስተቀር፤ ከኦሮሚያ የምስራቅና የምዕራብ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራና ጅማ፣ የቦረናና የባሌ የደቡብ ምዕራብ ዞኖች እንዲሁም ከሶማሌ የጎዴና የአፍዴር ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸው (ካርታ 3)።


ካርታ1   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ2   እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ3 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20 / 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በኦክቶበር የሁለተኛው አሥር ቀናት ሰሜንና የሰሜን ምሥራቅ እንዲሁም የመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ከነበራቸው የደመና ሽፋን በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ለጥቂት ቀናት አነስተኛ ዝናብ ያገኙ ቢሆንም ለዝናብ መፈጠርና መስፋፋት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከመዳከሙ አንጻር ብዙውን ጊዜ ደረቅ የአየር ሁኔታ ተዘውትሮባቸዋል። ይህም በመሆኑ በተለይም በመደበኛ ሁኔታ ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍል ዝናብ መውጫው ስለሆነና በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባው አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ቢሆንም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ለጥቂት ቀናት የተገኘው አነስተኛ እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና በመሰብሰብ ላይ ላሉና አልፎ አልፎ ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙ ሰብሎች አሉታዊ ተጽዕኖ ሲኖረው፤ዘግይተው ለተዘሩ በተለያ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙና ተገልብጦ በድጋሚ ለተዘሩ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት አወንታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል። በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ የነበረው እርጥበት በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር እሙን ነው። በአንጻሩ ደግሞ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ለደቡብና ለደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው በመሆኑ የተገኘዉ እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚካሄድባቸው በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ ክፍሎች ላይ ዘር ለመዝራት እንዲሁም በቆላማው አካባቢ ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽኦ እንደነበረው ይገመታል (ካርታ 4)።


ካርታ 4 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# <u>እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11-20/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
# <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ 11-20 ኦክቶብር 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ እርጥበት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በከፊል የምእራብ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ የደቡብ ምስራቅና የሰሜን ምስራቅ ተፋሰሶች ደግሞ መጠነኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው$ ይህንን ተከትሎ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ የአባይ መካከለኛውና ደቡባዊ ክፍል፣ አብዛኛው ኦሞጊቤ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆ፣ የገናሌዳዋ ምዕራባዊ አጋማሽና የታችኛው ተከዜ ኪስ ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል$ በተጨማሪም አብዛኛው አባይ፣ የገናሌዳዋ ምስራቃዊ አጋማሽና የዋቢሸበሌ ምዕራባዊው ክፍል ተዋሳኝ ተፋሰሶች፣ የታችኛው ባሮአኮቦና ተከዜ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው$ የተቀሩት የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅና የመካከለኛው የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል (ካርታ 5)$

ካርታ 5 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 11-20/2017 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 21-31/ 2017 የሚኖረው
# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በይበልጥ በምዕራብና በደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ እንደሚኖራቸውና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራል። ከዚህም ሌላ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከቀን ወደ ቀን በተለይም በደጋማ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ እየጨመረ እንደሚሄድ ይጠበቃል።

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ዞኖች ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ አርሲና ባሌ፣ የጉጂ እና የቦረና ዞኖች፤ የቤንሻንጉል ጉሙዝና የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የባህር ዳር ዙሪያ፣ ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ ዞን ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የወላይታ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የሲዳማና የጌዲዮ ዞኖች፣ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ሕዝቦች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በተጨማሪም በሶማሌ ክልል የሚገኙት የደገሀቡር፣ የፊቅ፣ የዋርዴር፣ የቀራሂ፣ አፍዴር፣ የጎዴ እና የሊበን ዞኖች በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።

# እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 21-31/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ከላይ በትንበያው ላይ እንደተገለፀው በሚቀጥለው የኦክቶበር ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት የእርጥበት ሁኔታው በደቡብና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚገኘዉ እርጥበት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ ለደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች አዲስ ለተዘሩ ሰብሎችም ሆነ በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን የውኃ አቅርቦት በመጠኑም ቢሆን ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፤ የእርጥበት ሁኔታው ወደ ደቡብና ወደ ደቡብ ምስራቅ የሚያደርገው መስፋፋት ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ጥሩ ጎን ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የዝናብ ወቅት ባልሆነባቸው አካባቢዎች በአብዛኛው ለግብርናው ዘርፍ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ዘግይተው ለተዘሩና በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የተሟላ እድገት የሚያስፈልጋቸውን የውኃ አቅርቦት ከማረጋገጥ አንፃር

አወንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለመሰብሰብና ለማከማችት መልካም አጋጣሚ ስለሚያገኙ ይህንኑ ለማከናወን የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ ምዝን የአየር እርጥበት በሚበዛበትና ደመናማ ሆኖ በሚቀይባቸው የመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለዋግ መፈጠር ምቹ ሁኔታዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ አርሶ አደሮች ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ሰብሎች እየደረሱ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የሰብል ስብሰባ እየተከናወነ ሲሆን፣ የሚጠበቀው እርጥበት ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ. ኤ. አ ከኦክቶበር 21-31/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት ውስጥ በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ በሚገኙ ተፋሰሶች በመካከለኛውና በታችኛው የተፋሰስ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ትንበያው ይጠቁማል፡፡ በዚህ መሰረት በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ገናሌዳዋና ዋቢሸበሌ፣ የአባይ ምዕራባዊ አጋማሽ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞጊቤና የታችኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ከመደበኛው ጋር ተቀራረበ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን የኦጋዴን ተፋሰሶች ደግሞ የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም ለዋቢሸበሌ፣ ለኦጋዴንና ለታችኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሶች የሚገኘው ዝናብ ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ የተፋሰሶቹ የእርጥበት ሁኔታ የተሻለ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የውሃ መገኘት ዘለቄታ እንዲኖረው በተለያየ መንገድ የዝናብ ውሃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ የሰሜንና የመካከለኛው ክፍል ተፋሰሶች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ፡፡